የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፳፯
አዲስ አበባ–ጥር ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 27
ADDIS ABABA–24th January, 2003

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፹፪/፲፱፻፺፭ ዓ.ም
የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅትን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ ገጽ ፪ሺ፷፰

## CONTENTS

Council of Ministers Regulations No. 82/2003
Ethiopian Airports Enterprise Establishment Council of Ministers Regulations ........ Page 2068

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፹፪/፲፱፻፺፭ ዓ.ም
### የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅትን ለማቋቋም
### የወጣ ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ በአንቀጽ ፵፯(፩) (ሀ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ ቁጥር "የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅትን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፹፪/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· መቋቋም

ሀ) የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅቱ" እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

ለ) ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል።

፫· ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን

በመንግሥት የሚሰየም አካል የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል።

### *COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS No. 82/2003*
### *REGULATIONS TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIAN AIRPORTS ENTERPRISE*

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the definition of powers and dutieis of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995 and Article 47(1) (a) of the Public Enterprise Proclamation No. 25/1992.

1. *Short Title*

These Regulations may be cited as the "Ethiopian Airports Enterprise Establishment Regulations No 82/2003"

2. *Establishment*

(a) There is hereby established the Ethiopian Airports Enterprise (hereinafter the "Enterprise") as a public enterprise.

(b) The Enterprise shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

3. *Supervising Authority*

A body to be designated by the Government shall be the Supervising Authority of the Enterprise.

፬. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የድርጅቱ ዋና መ/ቤት አዲስ አበባ ሆኖ ቅርንጫፍ መ/ቤቶች እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ሊያቋቁም ይችላል።

፭. <u>ዓላማ</u>

ሀ) በኢትዮጵያ ኤርፖርቶችን መገንባት፣ መጠገንና ማስተዳደር፣

ለ) ለአይሮፕላኖች፣ ለመንገደኞችና ለሌሎች ተጠቃሚዎች ደህንነቱ የተጠበቀ አስተማማኝና ቀልጣፋ የኤርፖርት አገልግሎት እንዲኖር ማድረግም በኤርፖርት ውስጥ ኤሮኖቲካል ያልሆኑ አገልግሎቶችን ማበረታታትና ማልማት፣

ሐ) የሚመለከተው አካል የሴኩሪቲ ሥራን የመሥራቱ ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ በብሔራዊ የአቪዬሽን ሴኩሪቲ ፕሮግራም መሠረት በኤርፖርቱ ውስጥ አስተማማኝ የሴኩሪቲ አገልግሎት እንዲኖር ማድረግ፣ የኤርፖርት ፋሲሊቴሽንን በተመለከተ መመሪያ ማውጣት፣ በበላይነት ማስተባበር መቆጣጠር፣

መ) ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎችን ማካሄድ፣

፮. <u>ካፒታል</u>

ለድርጅቱ የተፈቀደለት ካፒታል ብር ፪ ቢሊየን ፮፻፴፭ሚሊየን ፯፻፬ሺ፫፻፹፮ (ሁለት ቢሊየን ስድስት መቶ ሠላሳ አምስት ሚሊየን ሰባት መቶ አራት ሺህ ሦስት መቶ ሰማንያ ስድስት ብር) ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ብር ፩ ቢሊየን ፮፻፬ሚሊየን ፮፻፶፭ ሺ ፭፻፳፬ (አንድ ቢሊየን ስድስት መቶ አራት ሚሊየን ስድስት መቶ ሃምሣ አምስት ሺ አምስት መቶ ሃያ አራት ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል።

፯. <u>ኃላፊነት</u>

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

፰. <u>ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል።

፱. <u>የመብትና ግዴታ መተላለፍ</u>

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ ላይ የተጠቀሱ ኃላፊነቶችን በሚመለከት በአዋጅ ቁጥር ፩፻፲፩/፲፱፻፷፱ ይተዳደር የነበረው ለቀድሞ የአየር ትራንስፖርት ባለሥልጣን ተሰጥተው የነበሩ መብትና ግዴታዎች፣ በዚህ ደንብ ለድርጅቱ ተላልፏል።

፲. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

4. *Head Office*

The Enterprise shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

5. *Objectives*

(a) To construct maintain and administer aerodromes in Ethiopia;

(b) To provide safe, reliable and efficient airport service for aircraft; passengers and other users; to coordinate and develop in the aerodrome non aeronautical services.

(c) Subject to the performing of security activities by the relevant body, in accordance with the National Aviation Security Programme to ensure a reliable aviation security service in the aerodrome, to issue directives regarding airport facilitation, coordinate and control same.

(d) To engage in other related activities necessary for the attainment of its objectives.

6. *Capital*

The authorized capital of the Enterprise is Birr 2,635,704,386 (Two billion Six hundred Thirty Five million Seven hundred Four thousand Three hundred Eighty Six birr) of which birr 1,604,655,524 (One billion Six hundred Four million Six Hundred Fifty Five thousand Five hundred Twenty Four birr) is paid-up in cash and in kind.

7. *Liability*

The Enterprise shall not be liable beyond its total assets.

8. *Duration*

The Enterprise is established for an indefinite duration.

9. *Transfer of Rights & Obligations*

In relation to the duties and responsibilities mentioned under Article 5 of these Regulations, the rights and obligations of the Ethiopian Civil Aviation Authority given under proclamation No. 111/1977 are hereby transferred to the Enterprise.

10. *Effective Date*

These Regulations shall enter into force upon their publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 24th day of January 2003.

MELES ZENAWI
PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE